የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኢንስቲትዩቱ ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ

ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

<u>ወጪ</u>

1. ኢንስቲትዩቱን ለለቀቁ 2 ሰራተኞች በሥራ ገበታቸው ላልተገኙባቸው ቀናት በድምሩ ብር 5,586.00 አለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል።
2. ለተመራማሪዎች በተለያዩ ወራት ከተከፈለው አበል ተቀናሽ መደረግ የሚገባው፣ የሥራ ግብር ብር 1,753,234.22 ለሚመለከተው አካል ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል።
3. ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ አገር ለተላኩ ተመራማሪ የ8 ወራት ሙሉ ደመወዛቸው ብር 32,553.50 በብልጫ ወጪ መደረጉን እና ብር 33,800.00 የተመራማሪ አበል በመከፈሉ በድምሩ ብር 66,353.50 አለአግባብ ወጪ ሆኖ መገኘቱ ተረጋግጧል።

<u>ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

4. በተለያዩ የሂሳብ መደቦች የተያዘ በድምሩ ብር 8,573,950.94 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ተከፋይ ሂሳብ

5. በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 4,206,375.34 በወቅቱ ለባለመብቱ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡
6. የተለያዩ የላቦራቶሪ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፀም ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 138,506.88 እንዲሁም ከኢንስትቲዩቱ የቢሮ ኪራይ ክፍያ ገቢ መደረግ የሚገባው የተርን ኦቨር ታክስ ብር 4,800.00 በድምሩ ብር 143,306.88 ለሚመለከተው አካል ገቢ ያለመቀነሱን ተረጋግጧል፡፡

በጀት

7. ከመደበኛ በጀት ብር 3,833,736.89 ከበጀት በላይ ወጪ መደረጉን፤

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 አስከ 7 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፤ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- የመደበኛ በጀት ብር 6,248,015.15 እንዲሁም የካፒታል በጀት ብር 13,695,056.23 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱን፤
- የኢንስቲትዩቱ የተስተካከለ በጀት ብር 75,378,623.63 ሲሆን በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ተጨማሪ በጀት ብር 5,828,792.63 ውስጥ ብር 1,305,252.40 በሂሳብ መግለጫ ባለመያዙ የበጀት ዓመቱ የተስተካከለ በጀት ድምር ብር 74,073,371.23 ሆኖ ሪፖርት መደረጉ ተረጋግጧል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች

ንብረት

- ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር በተሟላ ሁኔታ አለመሰጠቱና በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት በተሰጠው አስተያየት መሠረት ማስተካከያ መደረጉ በድርጊት መርሀ ግብር ቢገለፅም እርምጃ አለመወሰዱን፣
- አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ በርካታ ንብረቶች ሳይወገዱ መገኘታቸውንና በ2008 በጀት ዓመትም እርምጃ ባለመወሰዱ ዕቃዎቹ ሳይወገዱ መገኘታቸው ተረጋግጧል፡፡
- 4 ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ከ2 ወር እስከ አራት ዓመት ያለአገልግሎት ቆመው መገኘታቸው፣
- ለረዥም ዓመታት አገልግሎት ሳይሰጡ የቆዩ 4 የተለያየ ሞዴል ተሽከርካሪዎች እንዲወገዱ አለመደረጋቸው፡ን፣
- 4 ሠራተኞች የሚገለገሉባቸውን የተለያዩ ንብረቶች ሳያስረክቡ ኢንስቲትዩን የለቀቁ መሆኑ ታውቋል፡፡
- የኢንስቲትዩቱ 7 ሹፌሮችና 6 የጥበቃ ሠራተኞች ተያዥ አቅርበው ተገቢውን የዋስትና ማረጋገጫ ሳይሰጡ በኢንስቲትዩቱ መቀጠራቸው ተረጋግጧል፡፡
- ለኢንስቲትዩቱ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች በተፈቀደው መዋቅር መሰረት የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ባለመሟላቱ በበቂ የሰው ኃይል አለመደራጀቱ ተረጋግጧል፡፡

እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2007 እና የ2008 በጀት ዓመት ግኝቶች፣

የ2008 በጀት ዓመት ግኝቶች፣

- ባልታወቀ ምክንያት በፈቃዳቸው ሥራቸውን የለቀቁ ሰራተኞች በአጠቃላይ በሥራ ገበታቸው ላይ ላልተገኙ ለሶስት ሠራተኞች በድምሩ ብር 4,119.64 የደመወዝ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣
- ለውሎ አበልና ለአልጋ ክፍያ ብር 1,707.00 በብልጫ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
- የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች ብር 2,727.27 ከተፈቀደላቸው የስልክ ሂሳብ ተመን በላይ ተጠቅመው የተገኙ መሆኑ፣

የ2007 በጀት ዓመት ግኝቶች፤

ለኮባልት ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማኅበር የተከፈለ ብር 2,346,295.09 መመዝገብ ካለበት በላይ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ

<u>ለሀብሪም ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማኅበር</u>

- ብር 151,171.03 በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ መገኘቱ፣
- ብር 101,617.50 በተሰብሳቢ ያልተያዘ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፣
- ብር 262,147.58 ያልተከፈለ መጣራት ያለበት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ መኖሩ፣
- ብር1,841,617,77 ለኮንስትራክሽን ድርጅቱ ለተፈጸመው ክፍያ የክፍያ ደረሰኝ (ማስረጃ) ያልቀረበለት መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የኢንስቲትዩቱን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የሪፓርቱ ዓላማ፣

የዚህ የሥራ አመራር ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ለማድረግ ነው ፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት ኢንስቲትዩቱ ባዘጋጃቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ / የኦዲት አስተያየት / ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፣

- የሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ የሠፈሩት አሀዞችና ሪፖርቶችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመር፣
- የሥራ አመራሩ የሂሣብ ሪፖርቶቹን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸውን ጉልህ ግምቶች እና ውሣኔዎችን መመዘን፣
- የሂሣብ አያያዝ ፖሊሲዎቹ ለሂሳብ ሪፓርቶቹ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣

ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሣብ ሪፖርቶቹ አግባብነት ያላቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የጸዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ የኦዲት አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሣብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በኢንስቲትዩቱ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሣብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሣብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የኢንስቲትዩቱ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **የወጪ ሂሳብ፤**

1.1.1 **ግኝት፤ ኢንስቲትዩቱን ለለቀቁ ሠራተኞች አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ፤**

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 12 የመንግስት ሠራተኞች ደመወዝ ክፍያ አፈፃፀም እንደሚያዘው ለደመወዝ ዝግጅት የሚከተሉት መመሪያዎች መሟላት አለባቸው፡፡ የመ/ቤቱ የሥራ ክፍሎች የክፍሉ ሠራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡ ይህንንም መረጃ ወር በገባ በ20ኛው ቀን የፋይናንስ ተግባር ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ያሳውቃል፡፡ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ የተገለፀው ቢኖርም ሠራተኛው ከ20ኛው እስከ 30ኛወ ባሉት ቀናት በሥራ ላይ ካልተገኘ ተረጋግጦ ከዚያው ወር ደመወዙ ተመላሽ ይደረጋል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ የኢንስቲትዩቱ የደመወዝ አከፋፈል ሥርዐት መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በተለያዩ ምክንያቶች ሥራቸውን በፈቃዳቸው የለቀቁ 2 ሰራተኞች በሥራ ገበታቸው ላልተገኙባቸው ቀናት በድምሩ ብር 5,586.00 አለአግባብ ተከፍሏቸው ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተራ. ቁ	የሠራተኛው ስም	የሂሳብ ማዘዣ ቁ	የተጣራ የወር ደመወዝ	አበል	የለቀቀቁበት ግዜ	የተከፈለበት ቀን	አለአግባብ የተከፈለ
1.	ወ/ት ሀይማኖት መብራቱ	0658945	1856.16		መጋቢት 4/09	ከመጋቢት 04- መጋቢት 30/09	1670.54
2.	ተካልኝ ይርጋ	875630	4941.48	2400	መጋቢት 15/09	መጋቢት 15- መጋቢት 30/09	3915.46
						ድምር	**5586.00**

1.1.2 **ስጋት፤**

- የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡
- የኢንስቲዩቱ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ላይውል ይችላል፡፡

1.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

አለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ክፍያዎች መመሪያን ተከትለው እንዲፈፀሙ ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

1.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

1.2.1 ግኝት፣ ለተመራማሪዎች ከተከፈለ አበል ተቀናሽ ያልተደረገ የሥራ ግብር፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባወጣው በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 የመንግስት መ/ቤቶችና ልማት ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች ድርጅቶችና ተቋማት ከተቀጣሪዎቻቸው ሊቀንሱት የሚገባውን የሥራ ግብር በተመለከተ ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ ለስራ ኃላፊዎች እና ለተመራማሪዎች በተለያዩ ወራት የተከፈለው አበል በየወሩ ከሚከፈለው ደመወዝ ጋር ተደምሮ የሥራ ግብር ብር 3,685,712.95 ተቀናሽ መደረግ ሲገባው፣ ከወር ደመወዝ ላይ ብቻ ብር 1,932,478.73 እንዲቀነስ በመደረጉ ብር 1,753,234.22 የሥራ ግብር ለሚመለከተው አካል ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የተከፈለበት ወር	የወር ደመወዝ	አበል	ድምር	መቀነስ የሚገባው የስራ ግብር	የተቀነሰ የስራ ግብር	ልዩነት
ሀምሌ	1,018,492.00	609,000.00	1,627,492.0	313,111.40	150,029.80	163,081.60
ነሀሴ	749,055.00	464,200.00	1,213,255.0	233,970.35	110,254.85	123,715.50
መስከረም	764,219.00	477,200.00	1,241,419.0	240,288.90	112,789.70	127,499.20
ጥቅምት	956,460.00	578,088.50	1,534,548.5	295,819.19	140,931.95	154,887.24
ህዳር	948,314.45	575,538.50	1,523,852.9	291,566.48	137,958.77	153,607.71
ታህሳስ	945,001.40	572,236.17	1,517,237.5	290,324.58	137,952.49	152,372.09
ጥር	951,876.50	578,059.50	1,529,936.0	293,462.72	139,344.75	154,117.97
የካቲት	1,183,689.50	581,609.50	1,762,667.0	354,883.37	190,867.40	164,015.97
መጋቢት	277,168.00	124,759.50	401,927.50	338,313.84	196,817.00	141,496.84
ሚያዚያ	1,203,511.40	520,950.00	1,724,886.4	345,009.54	205,448.19	139,561.35
ግንቦት	1,203,936.40	520,950.00	1,724,886.0	345,010 .00	205,448.19	139,561.35
ሰኔ	1,198,671.40	519,950.00	1,718,621.4	343,953.04	204,635.64	139,317.40
ድምር	11,400,395.05	6,122,541.67	17,520,729.72	3,685,712.95	1,932,478.73	1,753,234.22

1.2.2 ስጋት፣

- ተቀናሽ መደረግ የሚገባው ግብር ለሚመለከተው አካል ገቢ ባለመደረጉ የመንግስት የገቢ አሰባበሰብ ሥርዐት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡
- የወጣው የገቢ አሰባሰብ ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡

1.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የሥራ ግብር ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተመላሽ ተደርጎ ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ገቢ መደረግ ይገባዋል፡፡ ለወደፊቱም በደንቡ መሠረት ተቀናሽ እንዲደረግ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

ለተመራማሪዎች ከተከፈለ አበል ተቀናሽ ያልተደረገ የስራ ግብር በተመለከተ ከኢፌድሪ ጠቅላይ ሚንስቴር ጽ/ቤት በቁጥር መ100-2/813/2007 በቀን 02/07/2007 ለግብርና ሚንስቴር በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት የኢንስቲትዩቱ የስራ መሪዎች ተመራማሪዎችና የምርምር ረዳቶች የደመወዝና ጥቅማጥቅም ፓኬጅ አፈጻጸም መመሪያ ጽድቆ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ ሀምሌ 15/2008 ቀን በቁጥር ሲሰሚ 57.5/ጠ48/3/50 ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚንስቴር በተጻፈ ደብዳቤ እንድንሰራበት በተላከልን መመሪያ መሰረት የልጆች ት/ቤት ክፍያ፣ የሞባይል ስልክ አገልግሎት መግዣያ፣ የተንቀሳቃሽ የኢንተርኔት አገልግሎት ክፍያ የመኖሪያ ቤት አገልግሎት አበል በመመሪያው ግብር የማይከፈልበት መሆኑን የፈቀደ በመሆኑ ሳይከፈል ቆይቷል በሌላ በኩል የሲቪል ሰርቪስ ሚንስቴር በቁጥር ሲሰሚ 57.5/ጠ48/3/50 በቀን ሐምሌ 03/2007 መሰረት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት የመመሪያውን አፈጻጸም በተመለከተ ኢንስቲትዩቱ ተግባራዊ እንዲአደርግ የፈቀደ መሆኑን በወቅቱ አሳውቋል፡፡በመጨረሻ ከጠቅላይ ሚንስቴር ጽ/ቤት መስከረም 8/2010 በቁጥር መ100-2/813 በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት የገቢ ግብር መቀነስ ጀምረናል፡፡

1.2.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

በ2009 በጀት ዓመት ከተከፈለው አበል ተቀናሽ ያልተደረገውን የሥራ ግብር ለማስመለስ አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው እና ከኦዲቱ በኂላ የሚከፈለው አበል ግን ከደመወዝ ጋር እየተደመረ ተቀናሽ እንደሚደረግ ይህንንም በቋሚነት እንደሚተገብሩ እና በአሁኑ ወቅት ተቀናሽ ማድረግ መጀመራቸውን የኢንስቲትዩቱ ሥራ አመራር አባላት በኦዲቱ መውጫ ወቅት ገልፀዋል፡፡

በገቢ ግብር ህጉ ነፃ ካልተደረገ በስተቀር በማንኛውም አይነት ጥቅም ላይ ግብር መቀነስ እንደሚገባው በመግለፅ ተቀናሽ ሳይደረግ የሚፈፀመው ክፍያ እንዲቆም እና ክፍያው ከተፈፀመበት ግዜ ጀምሮ ያልተቀነሰው የግብር መጠን በውስጥ ኦዲቱ ተረገግጦ ተመላሽ እንዲደረግ የገ/ኢ/ት/ሚ/ር በቁጥር እንመ1/1/91 በቀን 29/12/2009 የገቢ ግብር ተቀናሽ

ያልተደረገባቸውን ጥቅማ ጥቅሞች በተመለከተ ለኢንስቲትዩቱ በፃፈው ደብዳቤ አሳውቋል፡፡ በመሆኑም በ2009 በጀት ዓመት ከተከፈለው አበል ተቀናሽ ያልተደረገው ሥራ ግብር በተላለፈው መመሪያ መሰረት ተመላሽ ተደርጎ ለሚመለከተው አካል ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.3.1 ግኝት፣ ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር ለሄዱ ሰራተኛ አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ፣

ከፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በቁጥር መ/9/ጠ49/2/56 በመስከረም 22/1993 በተላለፈ መመሪያ መሠረት ለትምህርት ወይም ለስልጠና እስከ 1 ወር ለሚቆይ ግዜ ወደ ውጭ ሀገር ለሚሄዱ የመንግሥት ሠራተኞች ሙሉ ደመወዛቸው እንዲከፈል ሆኖ ከ1 ወር በላይ ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር ለሚላኩት ግን ከተፈላጊ መረጃዎች ጋር ለኮሚሽኑ ቀርቦ ሲፈቀድ በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው እንዲከፈላቸው መወሰኑ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የኢንስቲትቱ ተመራማሪ የሆኑት አቶ ባሳዝን ፋንታሁን ለ2 ዓመት የከፍተኛ ትምህርት ወደ ሰኮላ ሳታና ዩኒቨርሲቲ በ14/02/2009 የተላኩ ሲሆን፣ ከህዳር--ሰኔ/2009 ለቆዩባቸው 8 ወራት ደመወዝ እና የተመራማሪ አበል የተከፈላቸው ሲሆን፣

- የግማሽ ወር ደመወዛቸው በድምሩ ብር 32,553.50 መከፈል ሲገባው ሙሉ ደመወዝ ብር 65,107.00 በመከፈሉ ብር 32,553.50 በብልጫ ወጪ መደረጉን፣
- አበል ብር 33,800.00 የተከፈላቸው መሆኑን፣

በድምሩ ብር 66,353.50 አለአግባብ ወጪ ሆኖ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

	የተከፈለበት ወር	የወር ደመወዝ	አበል	ድምር	መከፈል የሚገባው	
1	ህዳር/2009	7,284.00	4,600.00	11,884.00	3,642.00	8,242.00
2	ታህሳስ/2009	7,284.00	4,600.00	11,884.00	3,642.00	8,242.00
3	ጥር/2009	7,284.00	4,600.00	11,884.00	3,642.00	8,242.00
4	የካቲት/2009	8,651.00	4,000.00	12,651.00	4,325.50	8,325.50
5	መጋቢት/2009	8,651.00	4,000.00	12,651.00	4,325.50	8,325.50
6	ሚያዚያ/2009	8,651.00	4,000.00	12,651.00	4,325.50	8,325.50
7	ግንቦት/2009	8,651.00	4,000.00	12,651.00	4,325.50	8,325.50
8	ሰኔ/2009	8,651.00	4,000.00	12,651.00	4,325.50	8,325.50
	ድምር	65,107.00	33,800.00	98,907.00	32,553.50	66,353.50

1.3.2 ስጋት፣

- የወጣው መመሪያ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡
- መመሪያን ያልተከተለ ክፍያ በመፈፀሙ ኢንስቲትዩቱ ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡

1.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

አለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ሠራተኛ ተመላሽ መደረግ ይገባዋል፡፡ ለወደፊቱም በመመሪያው መሠረት ክፍያ እንዲፈፀም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሣብ፣

2.1 ግኝት፣

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሠራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ፣ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ተሰብሳቢ ሂሳብ በመመሪያው መሠረት በወቅቱ የሚወራረድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በሂሳብ መደብ 4203 የተያዘ ለሠራተኞች የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ብር 584,414.72 ከ7 ዓመታት በላይ፣
- በሂሳብ መደብ 4210 የተያዘ የመንግስት መ/ቤቶች ቅድመ ክፍያ ብር 48,487.70 ከ2 ዓመታት በላይ፣
- በሂሳብ መደብ 4211 የተያዘ ለግዥ ሠራተኞች ቅድመ ክፍያ ብር 12,913.70 ከ5 ዓመታት በላይ፣
- በሂሳብ መደብ 4251 የተያዘ ብር 3,035,714.71 ለህንፃ ተቋራጮች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ከ4 ዓመታት በላይ፣

- በሂሳብ መደብ 4253 የተያዘ እና ለዕቃ አቅራቢያዎች የተሰጠ ቅድመ ክፍያ ብር 4,220,301.72 ከ5 ዓመታት በላይ፣
- በሂሳብ መደብ 4274 ሌሎች ቅድመ ክፍያዎች ብር 672,118.39 ከ2 ዓመታት በላይ፣

በድምሩ ብር 8,573,950.94 በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

2.2 ስጋት፣

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፣ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያና ደንብ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ ቀርቦላቸው በወቅቱ እንዲወራረዱ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3. የተከፋይ ሂሳብ፣

3.1.1 ግኝት፣

የተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ የተከፈሉ ወይም የተወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በሂሳብ መደብ 5002 የተያዘ ልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች ብር 3,334,671.05 ከ1 ዓመት በላይ፣
- በሂሳብ መደብ 5003 የተያዘ የጡረታ መዋጮ ተከፋይ ብር 689,576.78 ከ1 ዓመት በላይ፣
- በሂሳብ መደብ 5006 የተያዘ ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ታክስ ብር 43,731.99 ከ3 ወራት በላይ፣
- በሂሳብ መደብ 5021 የተያዘ ለሰራተኞች ተከፋይ ሂሳብ ብር 13,196.66 ከ3 ወራት በላይ፣

- በሂሳብ መደብ 5059 የተያዘ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 125,198.86 ከ3 ወራት በላይ፣

በድምሩ ብር 4,206,375.34 በወቅቱ ለባለመብቱ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡

3.1.2 ስጋት፣

የተከፋይ ሂሳብ ለባለመብቱ ድርጅት፣ መ/ቤት ወይም ግለሰብ በወቅቱ አለመተላለፉ ገንዘቡ ለታቀደለት ዓላማ እንዳይውል ሊያደርግ እና በበጀት አጠቃቀም ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

3.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ለወደፊቱም በተከፋይ ሂሳብ ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

3.2.1 ግኝት፣ ተቀናሽ ያልተደረገና ለሚመለከተው አካል ያልተከፈለ ታክስ፣

በገኘው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 5 ተራ ቁጥር 1 የአንድ ጊዜ ግብይት ዋጋ ከብር 5,000.00 በላይ ሲሆን፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ተደርጎ ለገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት እንዲከፈል ያዛል፡፡ በተጨማሪም በአንቀጽ 6 ቁጥር 4 ማንኛውም ወኪል ከግብይቱ ቀንሶ ያስቀረውን ታክስ በ30 ቀናት ውስጥ ገቢ ባያደርግ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 90 መሠረት አስተዳደራዊ መቀጫ እና የወንጀል ቅጣቶች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 3. ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት አካል በወሩ ውስጥ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ቀሪ መደረግ የሚገባውን ሂሳብ ከወሩ መጨረሻ ጀምሮ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የኢንስቲትዩቱ የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፣

- የተለያዩ የላቦራቶሪ ዕቃዎች ከወሊን ትሬዴንግ ኃ/የተ/ የግል ማህበር ለተገዙበት ብር 1,061,886.16 የተከፈለ ሲሆን፣

- በ22/11/2008 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0691756 በወጪ ከተያዘው ብር 966,886.16 ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 126,115.58፣
- በ27/10/2009 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 126012 በወጪ ከተያዘው ብር 95,000.00 ተቀናሽ መደረግ የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 12,391.30፣

በድምሩ ብር 138,506.88 ለሚመለከተው አካል ገቢ መደረግ ሲገባው ተቀናሽ ሳይደረግ ሙሉ ክፍያ ለአቅራቢው እንዲከፈል መደረጉን፣

- ➤ ኢንስትቲዩቱ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የቢሮ ኪራይ ውል ሲፈፅም፣ በውሉ አንቀጽ 3 የኪራይ ተመንና አከፋፈልን በተመለከተ በቁጥር 3.1 እንደተገለፀው ወርሃዊ የኪራይ ተመን ብር 8,000.00 እና የተርን ኦቨር ታክስ ብር 800.00 በድምሩ ብር 8,800.00 ኢንስቲትዩቱ በየወሩ የሚከፍል መሆኑንና የ6 ወር ኪራይ ብር 52,800.00 በቅድሚያ እንዲከፍል ስምምነት የተደረገ ሲሆን፣ ከኪራይ ጋር በተያያዘ ያሉትን ቀረጥ፣ ግብር፣ ታክስና የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ የመክፈል ግዴታ የአከራይ መሆኑ በውሉ ቢገለፅም የተርን ኦቨር ታክስ ብር 4,800.00 አከራይ ለገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ለመክፈሉ ደረሰኝ ባለመቅረቡ ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ አለመቻሉን፣

በጠቅላላው ብር 143,306.88 ለገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት ገቢ አለመደረጉን ተረጋግጧል፡፡

3.2.2 ስጋት፣

- መንግሥት ሊያገኝ የሚገባው ገቢ በወቅቱ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡
- የወጣው መመሪያና አዋጅ ተግባራዊ ላይደረግ ይችላል፡፡

3.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የላብራቶሪ ዕቃዎችን ግዥ በተመለከተ የቀረበው ማስረጃ ድርጅቱ የዕቃዎቹ አቅራቢ ለመሆኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንጂ ከታክስ ከፋይነት ነፃ መሆኑን የሚገልፅ ባለመሆኑ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም፡፡ ከቢሮ ኪራይ ተቀናሽ ተደርጎ መከፈል የሚገባውን የተርን ኦቨርና የዊዝሆልዲንግ ተቀናሽ ሂሳብን በተመለከተ የተሰጠው ምላሽ ከግኝቱ ጋር የማይዛመድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ተቀናሽ ያላደረገውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ከአቅራቢው ድርጅት እንዲሁም የተርን ኦቨር እና የተከፋይ ተቀናሽ ታክስን ከቢሮ አከራዩ ድርጅት ተመላሽ በማድረግ ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

4. በጀት፣

4.1.1 ግኝት፣ ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት እና ከበጀት በላይ የወጣ፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የኢንስቲትዩቱ የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ለመደበኛ ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣ ብር **3,833,736.89** ከበጀት በላይ ወጪ መደረጉን፤ እንዲሁም በየሂሳብ መደቦቹ ከ10% በላይ ብር 6,248,015.15 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱን፣
- ለካፒታል ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣ በየሂሳብ መደቦቹ ከ10% በላይ ብር **13,695,056.23** ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱን፤

ተረጋግጧል፡፡

4.1.2 ስጋት፣

- በበጀት ዓመቱ ተራፊ በጀት መገኘት በሌሎች መ/ቤቶች ሊሠራበት የሚችለውን በጀት በኢንስቲትዩቱ ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡
- የተፈቀደው በጀቱ በዕቅዱ መሠረት ተግባራዊ አለመደረጉ የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

- ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መደረጉ ደንብና መመሪያን እንዳይከበር ከማድረጉ በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

4.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ከበጀት በላይ ወጪ ለመደረጉ የተሰጠው ምላሽ፣

- በበጀት ዓመቱ ብዛት ያላቸው ተመራማሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በመቀጠራቸው፣ የሥራ መስክ በመስፋፋቱ የኢንተርኔትና የስልክ ፍጆታ ከፍተኛ በመሆኑ፣ ተጨማሪ ቢሮዎች በመከፈታቸው፣ የደመወዝ ማስተካከያ በመደረጉ፣ እንዲሁም አበልና ከደመወዝ ጋር ተያያዥ የሆኑ ወጪዎች ከፍተኛ መሆናቸው ነው በማለት ምላሽ ቢሰጥም፣ ኢንስቲትዩቱ ለገጠመው የበጀት እጥረት ተጨማሪ በጀት ጠይቆ የተፈቀደለት በመሆኑና በተፈቀደው ተጨማሪ በጀት ወጪውን መሸፈን ባለመቻሉ ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በ2008 በጀት ዓመት ለተፈፀመ የኬሚካል ግዥ አስቀድሞ በዕቅድ ከተያዘው እና በወቅቱ ባለመከፈሉ ተመላሽ የተደረገውን በጀት በማስፈቀድ ክፍያ መፈፀም ሲገባ፣ ከ2009 በጀት ላይ እንዲከፈል መደረጉ ተረጋግጧል፡፡
- ጂን ባንኮችና ሌሎች የክልል ማዕከላትን ለማደራጀትና ለማስፋፋት ተጨማሪ በጀት የተፈቀደለት በመሆኑ ወጪው በዚሁ በጀት መሸፈን ሲገባው፣ ከበጀት በላይ ወጪ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡
- በሂሳብ መደብ 6241 ከበጀት በላይ ወጪ ለመደረጉ የተሰጠው ምላሽ የሥራ መስክ በመስፋፋቱና ሠራተኛ በብዛት በመቀጠሩ ምክንያት መሆኑ የተገለፀ ሲሆን፣ በዚህ የወጪ አርዕስት ወጪ የሚደረገው ለመኪናዎችና ተሽከርካሪዎች ጥገና በመሆኑ የተሰጠው ምክንያት ከክፍያው ጋር የማይዛመድ መሆኑን፣

በአጠቃላይ የበጀት ዕቅዱ በጥናት ላይ የተመሠረተ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በመሆኑም በየወሩ በሥራ ክፍሉ በሚቀርበው የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት መሠረት ተራፊው በጀት በመ/ቤቱ ስም ተይዞ እንዳይቆይ በሌሎች መ/ቤቶች እንዲሰራበት ሪፖርት እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ኢንስቲትዩቱ የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስና በጀት አዋጅ መሠረት እንዲጠቀም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

4.2.1 ግኝት፣ በበጀት ዓመቱ የሂሳብ መግለጫ ያልተያዘ ተጨማሪ በጀት፣

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል 4 ቁጥር 1 እና 3 የመንግሥት መ/ቤቶች የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀትን አጠቃቀም ሪፖርት በየወሩ እና በየሩብ ዓመቱ በሂሳብ አመዘጋገብና ሪፖርት አቀራረብ መመሪያ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር እንዲያቀርቡ ያዛል፡፡ በተጨማሪም በመመሪያው ክፍል 3 ቁጥር 2 ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ ለመቆጣጠር እንዲችል የበጀት መቆጣጠሪያ መዝገብ ሊኖረው እንደሚገባና ይህም መዝገብ ለመ/ቤቱ የተፈቀደውን የተጨማሪ በጀት ዝርዝር፣ የተፈቀደውን የበጀት ዝውውርና የተስተካክለ በጀት የሚያሳይ መሆን እንደሚገባው ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የኢንስቲትዩቱ የተስተካከለ በጀት ብር 75,378,623.63 ሲሆን በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ተጨማሪ በጀት ብር 5,828,792.63 ውስጥ ብር 1,305,252.40 በሂሳብ መግለጫ ባለመያዙ የበጀት ዓመቱ የተስተካከለ በጀት ድምር ብር 74,073,371.23 ሆኖ ሪፖርት መደረጉ ተረጋግጧል፡፡

4.2.2 ስጋት፣

- ኢንስቲትዩቱ ከተፈቀደለት በጀት የተጠቀመውን በትክክል ለመረዳት አዳጋች ይሆናል፡፡

4.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በመመሪያው መሠረት በበጀት ዓመቱ የተፈቀደው እና በተጨማሪ በዝውውር ገቢ የተደረገው በጀት በአግባቡ በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ እንዲገለፅ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

5. ንብረት፣

5.1.1 ግኝት፣ የኢንስቲትዩቱን የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ በተመለከተ፣

የኢንስቲትዩቱ የንብረት አስተዳደር እና አጠባበቅ በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር በተሟላ ሁኔታ አለመስጠቱና በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ መወሰዱን በድርጊት መርሀ ግብር ቢገለፅም እርምጃ አለመወሰዱን፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒዩተሮች፣ የብረት ጠረጴዛ፣ ወንበሮች፣ የመኪና ጎማዎች፣ ሁለት ፍሪጅ፣ የዘር መቆጣጠሪያ ዕቃዎች፣ የፎቶ ኮፒ ማሽን፣ የውሀ ማጣሪያ፣ ስልክ፣ የመደመሪያ ማሽን፣ ሻተር፣ ምጣድ፣ ሚዛን እና በርካታ የተለያዩ ንብረቶች እንዲሁም ሶስት ተሸከርካሪ መኪና እና አንድ ሞተር ሳይክል ሳይወገዱ መገኘታቸውንና በ2008 በጀት ዓመትም እርምጃ ባለመወሰዱ ዕቃዎቹ ሳይወገዱ መገኘታቸው ተረጋግጧል፡፡

<u>**የተሽከርካሪዎች አያያዝ በተመለከተ፣**</u>

- 4 ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ከ2 ወር እስከ አራት ዓመት ያለአገልግሎት ቆመው መገኘታቸው፣
- ለረዥም ዓመታት አገልግሎት ሳይሰጡ የቆዩ 4 የተለያየ ሞዴል ተሽከርካሪዎች እንዲወገዱ አለመደረጋቸው፡ን፣
- አንድ ተሳቢ ተሽከርካሪ ሊብሬው ቢኖርም፣ ተሽከርካሪውን (ጎታቹን) መሪና ሞተር የሌለው በአካል ማግኘት ያልተቻለ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

<u>**ኢንስቲትዩቱን ከለቀቁ ሠራተኞች ተመላሽ መደረግ የሚገባቸውን ንብረቶች በተመለከተ፣**</u>

ኢንስቲትዩቱን የሚለቁ ሠራተኞች እጅ የሚገኘውን ንብረት በአግባቡ ለመ/ቤቱ መመለሳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ 4 ሠራተኞች የሚገለገሉባቸውን የተለያዩ ንብረቶች ሳያስረክቡ ኢንስቲትዩን የለቀቁ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የሰራተኛው ስም	የዕቃው አይነት	መለያ ቁጥር	ሞ/22 ቁ
1	ጌታቸው ሲሳይ	ላፕቶፕ ኮምፒውተር ቶሺባ	ZB197192W	
2	ተክሌ ሂርጳ	ፍላሽ		440799
		ጠረጴዛ ባለ3 መሳቢያ		441247
		ላፕቶፕ ኮምፒውተር ከነቦርሳው	zB225093.W	171077
3	ሀብታሙ ፀጋዬ	ባለ 4 መሳቢያ ፋይል ካቢኔት		440284
4	ቴዎድሮስ ያዛቸው	አትክልት መቀስ		441238

		የሳር ማጭድ ማሽን		441332
		መኮትኮቻ		441241
		ጋሪ፣ መቀስ፣ አካፋ፣ዶማ፣ባለ 3 ጡት መኮትኮቻ፣ ገሶ ያገለገለ		441241 440289

5.1.2 ስጋት፣

- በንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ መሠረት ንብረቶች በአግባቡ ባለመጠበቃቸው ለብክነት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡
- ተገቢው የንብረት ምዝገባ እና አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊ ባለመደረጉ ኢንስቲትዩቱ ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ ይችላል፡፡
- በመንግሥት ውስን ሀብት የተገዙት ንብረቶች ለግለሰቦች ጥቅም በመዋላቸው የመንግሥት ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ ሳይውል ይችላል፡፡

5.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተለይተው እንዲወገዱ እና ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ዕቃዎች ለአገልግሎት እንዲበቁ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ለቢሮ አገልግሎት እንዲውሉ የተሰጡ ቋሚ ዕቃዎች ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ እንዲደረጉ ተገቢው ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

5.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

5.2.1 ግኝት፣ ዋስትና ሳያስይዙ የኢንስቲትዩቱን ንብረት የተረከቡ ሠራተኞችን በተመለከተ፣

በመንግሥት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዐት መመሪያ ቁጥር 11/2003 መሠረት ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር እና የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጆች እና እነዚህን አዋጆች ለማስፈፀም በወጡ ደንቦች እንዲሁም መመሪያዎች ስለመንግት ገንዘብና ንብረት አጠባበቅ፣ አመዘጋገብና አያያዝ፣ ስለወጪ አከፋፈልና ጥቃቅን ወጪዎች የተወሰነ ገንዘብ እንዲሁም በግዥ ላይ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በገንዘብ ያዥነት፣ ሰብሳቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሠራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲሰጡ ወይም እንዲያቀርቡ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ይህም መመሪያ የመንግሥት መሥሪ ቤት ተብለው በተመለከቱት

ሁሉ ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የኢንስቲትዩቱ የንብረት አያያዝ ሥርዐት መመሪያን የተከተለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የኢንስቲትዩቱ 7 ሹፌሮችና 6 የጥበቃ ሠራተኞች ተያዥ አቅርበው ተገቢውን የዋስትና ማረጋገጫ ሳይሰጡ በኢንስቲትዩቱ መቀጠራቸው ተረጋግጧል፡፡ በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም በተለያዩ ክፍሎች የሚሰሩ ሠራተኞች ዋስትና ወይም ተያዥ ሳይኖራቸው የተለያዩ ንብረቶችን እንዲረከቡ መደረጉ አግባብ አለመሆኑ ተገልፆ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት ቢሰጥም፣ የሥራ አመራሩ እርምጃ ባለመውሰዱ በ2009 በጀት ዓመትም መታየቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

5.2.2 <u>ስጋት፣</u>

- ለተረከቧቸው ንብረቶች ዋስትና ባለማስያዛቸው ተጠያቂነታቸውን ለማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል፡፡
- የወጣው መመሪያ ተግባራዊ ሳይደረግ ይችላል፡፡

5.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በኢንስቲትዩቱ ተቀጥረው በተለያዩ የሥራ ክፍሎች በመሥራት ላይ የሚገኙ ሠራተኞች ለተረከቧቸው ንብረቶች ዋሰትናነት እንዲያስይዙ እና በስማቸው ለተያዙት ንብረቶች ኃላፊነትን እንዲወስዱ የሚያደርግ የአሰራር ሥርዐት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

5.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

6 <u>ልዩ ልዩ፣</u>

6.1.1 <u>ግኝት፣ በቅጥርና በደረጃ ዕድገት ያልተሟሉ ክፍት የሥራ መደቦችን በተመለከተ፣</u>

የመንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች ቁጥር 8/2008 የመንግስት መስሪያ ቤት የሰው ኃይሉን በቅጥር ለማሟላት፣ ለማስተዋወቅ፣ ለማሰልጠን፣ ለመቆጣጠር፣ ለመገምገም፣ ለማማከር፣ ለማሳደግ፣ ለመካስ፣ በዲሲፕሊን ለመቅጣት፣ ለማሰናበት እና ለመሳሰሉት አስተዳደራዊ ሥራዎች ተስማሚ ፖሊሲዎችንና የአፈጻጸም መመሪያዎች ሊኖሩት እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ለኢንስቲትዩቱ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች በተፈቀደው መዋቅር መሰረት የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት 736 ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ የሚገኙ 566 ሠራተኞች በመሆናቸው 170 (23.09%) ክፍት የሥራ

መደቦች ሠራተኞች ባለመቀጠራቸው ኢንስቲትዩቱ በበቂ የሰው ኃይል አለመደራጀቱ ተረጋግጧል፡፡

6.1.2 ስጋት፣

- ኢንስቲትዩቱ በበቂ የሰው ኃይል ባለመደራጀቱ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሚጠበቅበትን ተግባር በአግባቡ እንዳይወጣ ያደርገዋል፡፡
- ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመለትን ዓላማ ላያሳካ ይችላል፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ኢንስቲትዩቱ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲሟሉ ማድረግ ይጠበታል፡፡

6.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

6.2.1 ግኝት፣ እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2007 እና የ2008 በጀት ዓመት ግኝቶች፣

➢ **የ2008 በጀት ዓመት ግኝቶች፣**

- ባልታወቀ ምክንያት በፈቃዳቸው ሥራቸውን የለቀቁ ሰራተኞች በአጠቃላይ በሥራ ገበታቸው ላይ ላልተገኙ ለሶስት ሠራተኞች በድምሩ ብር 4,119.64 የደመወዝ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣
- ለውሎ አበልና ለአልጋ ክፍያ ብር 1,707.00 በብልጫ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
- የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች ብር 2,727.27 ከተፈቀደላቸው የስልክ ሂሳብ ተመን በላይ ተጠቅመው የተገኙ መሆኑ፣

➢ **የ2007 በጀት ዓመት ግኝቶች፤**

በኢንስትቲዩቱ ለህንፃ ተkራጭ የሚፈጸም ክፍያ በውሉ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

ለኮባልት ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማኅበር

- ብር 2,346,295.09 መመዝገብ ካለበት በላይ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ

ለህብሪም ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማኅበር

- ብር 151,171.03 በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ መገኘቱ፣
- ብር 101,617.50 በተሰብሳቢ ያልተያዘ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፣
- ብር 262,147.58 ያልተከፈለ መጣራት ያለበት የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ መኖሩ፣

- ብር1,841,617,77 ለኮንስትራክሽን ድርጅቱ ለተፈጸመው ክፍያ የክፍያ ደረሰኝ (ማስረጃ) ያልቀረበለት መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

6.2.2 ስጋት፣

ኢንስቲትዩቱ ለኦዲት ሪፖርት የሚሰጠውን ትኩረት ሊያሳንሰው ይችላል፡፡ በሪፖርት በሚሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶች መሰረት እርምጃ ያለመውሰድ ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል፡፡

6.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወስዱ በኦዲቱ ወቅት በተሰጠው ምላሽ እና በበጀት ዓመቱ በቀረበው የኦዲት ግኝት የድርጊት መርሀ ግብር ቢገለፅም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት እስከ ጥቅምት 30/2010 እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት ተገቢው እርምጃ ለመወሰዱ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚገባው በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

6.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፣

የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!!